# አነጋጋሪው የጠ/ሚ ኃይለማርያም ደሳለኝ ቃለምልልስ

(ሰንደቅ 8ኛ ዓመት ቁጥር 372 ጥቅምት 14 2005)

- ባቤታቸው ኤርትራዊ አለመሆናቸውን አረጋገጡ
- የንጉስ ጦር ዘር አይደለሁም ብለዋል
- ቃለ መሃላ በሚፈፅሙበት ወቅት ዘላለማዊ ክብር ለጠ/ሚኒስትራችን ባሏት ቃል ተፀፅተዋል፡፡

«ባለቤቴ ሁለቱም ወላጆቿ የወላይታ ብሔር ተወላጆች ናቸው፡፡ ወላይታ… በኤርትራ ክልል ውስጥ ነው ካልተባለ በቀር እኔም ባለቤቴም ወላይታና ኢትዮጵያውያን ነን…» **ጠ/ሚኒስትር ኃ/መርያም ደሳለኝ**

*መሰረታቸውን በውጪ አገር ያደረጉ የኢትዮጵያውያን ድረ-ገፅ ሰሞኑን የጠ/ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ ባለቤት ቀዳማዊት እመቤት ሮማን ተስፋዬ ኤርትራዊ መሆናቸውን ሲፅፉ ሰንብተዋል፡፡ የቀድሞ ጠ/ሚኒስተር አቶ መለስ ዜናዊ እናታቸው «አዲቋላ» (ኤርትራ) በመወለዳቸው ለኤርትራ ሊወግኑ ይችላሉ የሚል አሉባልታ እደሚናፈሰው ሁሉ በተመሳሳይ ሁኔታ አቶ ኃይለማርያም በለቤታቸው ኤርትራዊ በመሆናቸው ወደ ኤርትራ ያደላሉ ለማለት ከወዲሁ የተፈለገ ይመስላል፡፡*

*ወ/ሮ ሮማንን ኤርትራዊ ብሎ ለመፈረጅ ድረ-ገፆቹ የደፈሩት ለሁለተኛ ሴት ልጃቸው የሰጡት «ዮሃና» የሚል ስም ነው፡፡ «ዮናሃ» ብዙ ኤርትራዊያን የሚጠቀሙበት ስም መሆኑንና ትርጉሙም «እንኳን ቀናህ» (congratulation) እንደማለት ነው፡፡ ሁለተኛ ሴት ልጃቸው ዮሃና በአሁኑ ወቅት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የምህንድስና ሁለተኛ አመት ተማሪ ስትሆን በቤተ ክርስቲያንም እግዚአብሔርን የምታገለግል ትሁት ወጣት ናት፡፡ እንዲሁም በቤተክርስቲያኗ ደንብ መሰረት ቀዳማዊ እመቤት ወ/ሮ ሮማን ተስፋዬ እንዲሁም ዮሃናን እና እህቶቿ ሜክአፕ የተለያዩ ጌጣጌጦችን በሰውነታቸው ላይ እንደማያጠልቁ አቶ ኃ/ማርያም ለዘጋቢው ነግረውታል፡፡*

*«ዮሃና» የእብራይስጥ ቃል ነው፡፡ የእግዚአብሔር ስጦታ ወይም ፀጋ እደማለት ነው፡፡ አቶ ኃይለማርያም እና ባለቤታቸው ሮማን ለሁለተኛ ሴት ልጃቸው ስም ሲያወጡ ይህንኑ የእግዚአብሔር ቃል ግምት ውስጥ እንዳስገቡ መገመት ይቻላል፡፡ አቶ ኃይለማርያም በቅርቡ በጠ/ሚኒስትርነት ከተሾሙ በኋላ ለአንድ የሃይማኖት ሚዲያ በሰጡት ቃለ ምልልስ ባለቤታቸው በአባታቸውም በእናታቸውም የወላይታ ብሔር ተወላጅ መሆናቸውን ማረጋገጫ ሰጥተዋል፡፡ ቃለ ምልልሱ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡*

**ጥያቄ፡-** ክቡር ጠ/ሚኒተር አቶ ኃ/ማርያም አዲሱን ስልጣን እንዴት አዩት?

**ጠ/ሚኒስትር ኃ/መርያም፡-** እንግዲህ ከጌታ ጋር ሁሉንም ለመወጣት ተያይዘናል ያስጀመረን ጌታ ከግቡ ያደርሰናል የሚል ዕምነት አለኝ፡፡

**ጥያቄ፡-** እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ አልፎ አልፎ በከባድ ጥበቃ እየታጀቡ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንደሚሄዱ ባለቤቴ ትነግረኛለች ፡ ይህ እውነት ነው ?

**ጠ/ሚኒስትር ኃ/መርያም፡-** አዎን ለእኔና ለቤተሰቤ መሰረታችን እምነታችን ስለሆነ የዘወትር ሕይወታችን በቤተክርስቲያን ዙሪያ ነው፡፡ ጊዜ ሳገኝ አልፎ አልፎ እሁድን እንደምንም ቤተ ክርስቲያን (ቸርች) ለመሄድ ጥረት አድርጋለሁ፡፡ ካልሆነም ቄሶችን የቤተክርስቲያን አገልግዮች እኛ ቤት ድረስ እየመጡ የጌታን ቃል ያካፍሉናል፡፡

በቤታችን ውስጥ ግን ማታ ማታ ሁሌም የቤተሰብ ፕሮግራም እናደርጋለን፡፡ እንዘምራለን እናመልካለን መፅሃፍ ቅዱስ ከፍተን ሁላችንም ጥቅሶች አንብበን ተንበርክከን ፀሎት አድርገን ወደ መኝታ እንሄዳለን፡፡

**ጥያቄ፡-** አብረዋችሁ የሚሰሩ የኢህአዴግ ሰዎች ባልሳሳት ኤትየስት /ኃይማኖት አልባ/ ናቸው ሲባል እሰማለሁ፡፡ ይህ በእርሶ ስራዎች ላይ ፈተና አልሆነብዎትም ?

**ጠ/ሚኒስትር ኃ/መርያም**፡- በኢህአዴግ ፖሊሲ ኃይማኖት የግል አድርገህ በውስጥህ የምትይዘው ነገር ስለሆነ በአመራር ውስጥ ያለነው ራሳችንን ኃይማኖት በሌሎቹ ላይ ማንፀባረቅ ወይም ጫና ማድረግ ባይፈቀድልንም አንዳንዶቹ ስለእኔ እምነት ለማወቅ የሚፈልጉት ነገር ሲኖን ከመጠየቅ ወደኋላ ብለው አያውቁም፡፡ እኔም በመጠኑ መንገድ ለማስረዳት እሞክራለሁ፡፡ በተረፈ ከስራ ጓዶቼም ጋር ሆነ ብለን በስራ ቦታ ስለ ግል እምነት አንስተን ተወያይተን አናውቅም፡፡ ይህን ስል በአገሪቱ በኃይማኖቶች ዙሪያ በሚፈጠሩት ችግሮች መንግስት ምን ማድረግ አለበት በሚለው ላይ አንወያይም ማለቴ አይደለም፡፡

**ጥያቄ**፡- ለመሆኑ ከአቶ መለስ ዜናዊ ጋር ስለ ኃይማኖትዎ አንስተው ተወያይተውበት ያውቃሉ ?

**ጠ/ሚኒስትር ኃ/መርያም**፡- ስለ ኃይማኖት አንስተን ተወያይተናል፡፡ ግን ውይይቱ ጠቅለል ባለ መልክ ስለሁሉም ኃይማኖቶች እንጂ ስለእኔ ወይም ስለ አንድ ኃይማኖት አይደለም፡፡ እሳቸው ኃይማኖቶች ተቻችለውና ተከባብረው የሚኖርባትን አገር ማየት ነበር ራዕያቸው፡፡ የኃይማኖት ጽንፈኝነት ሁሌም መዋጋት ያለብን ነገሮች እንደሆኑ ይናገራሉ፡፡

**ጥያቄ**፡- እንደሚታወቀው ከተማሪነት ዕድሜ ጀምሮ በጣም የተመሰጡ ኃይማኖተኛ ነዎት ፖለቲከኛ ሲሆኑ ብዙ ኃይማኖትን የሚፃረር ውሳኔዎና እርምጃዎች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ በዚህ አንፃር እንዴት ነው ወደ ፖለቲካው መድረክ ሲወጡ ያጋጠምዎት መሰናክል የለም ?

**ጠ/ሚኒስትር ኃ/መርያም**፡- የኢህአዴግ ፖሊሲ አብዛኛው ከምከተለው ኃይማኖት ጋር ቢቀራረብ እንጂ አይፃረርም፡፡ ይሄውም አለመስረቅ አለመዋሸት፣ ከጉቦኝነት ከአሻጥር በጠራ ስራ በቅንነት ወገንና አገርን ማገልገል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው፡፡ መጽፍ ቅዱስ ፈርሐ እግዚአብሄር ስንሆንና መልካም ሕሊና ሲኖረን በነገር ሁሉ መልካም ነገርን ማፍለቅ እንደምንችል ይነገረናል፡፡

**ጥያቄ**፡- አንዳንድ ሰዎች የእርስዎ እዚህ ድረስ መድረስ የእግዚአብሔር ፈቃድ ወይም የእግዚአብሔር ስራ ነው ይላሉ፣ የእርስዎ አስተያየት ምንድን ነው ?

**ጠ/ሚኒስትር ኃ/መርያም**፡- ማንኛውም ሰው አገርን ወደሚመራበት ደረጃ ሲደርስ የእግዚአብሔር ፈቃድ አለበት ብዬ አምናለሁ፡፡ ልዩነቱ እግዚአብሔርን የሚያውቅና በልቡ ፈጣሪውን መከታ የሚያደርግ እንዲሁም የእግዚአብሔርን ጥበብና ፊት የሚሻ ሰው በሕይወቱም ሆነ በስራው ሁሉ እግዚአብሄር ይቀድማል፡፡ እግዚአብሄርን የማይፈራ በራሱ ጥበብ ልንቀሳቀስ ከሚለው ጋር እግዚአብሔር ጋይድ ወይም መሪው ሊሆነው አይችልም፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ዓለም ስንኖር በስጋ ጥበብ ሳይሆን በእግዚአብሔር ፀጋ ጥበብና ቅድስና ስንመላለስ ሕሊናችን ምስክር ነው፡፡ ትምክህታችንም ደግሞ ይህ ብቻ ነው ብሏልና፡፡ ስለዚህ እኔ አኮምፕሊሽ አድርጌአለሁ ዓላማዬ ግቤን መታ ልል ምንም ምክንያት የኝም፡፡ ይልቁንስ ለአገሬና ሕዝቤ የበኩሌን ምን ላድርግ ብዬ አስባለው፡፡ ክርስትና በሕይወቴ ብዙ ጥንካሬዎችን የሰጠኝም በብዙ ውጥረቶችና ችግሮች መሀል መንፈሳዊ ትምክህት አለኝ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምክህት ከሌላው ዓይነት ትምክህት ለየት ይላል ሌላኛው ዓይነት ትምክህት በእጅ ባለው ነገር ወይም በራስ እውቀት መኩራራት (መቦሰት) ሲሆን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቡስት ግን በሃያሉ በአምላክ ፍፁም መታመን ው፡፡

**ጥያቄ**፡- ለምሳሌ አቶ መለስ አማኝ ወይም ክርስቲያን አልነበሩምና እሳቸው እግዚአብሄር ጋይድ ሆኖ አያውቅም ማለት ይቻላል?

**ጠ/ሚኒትር ኃ/ማርያም**፡- እሳቸው ክርስቲያን አልነበሩም ማለት አይቻልም፡፡ የእምነታቸው ጉዳይ የግል ስለሆነ እሱን ከፈጣሪና ከእሳቸው ጋር ያለውን ግንኙነት ደጅ ብናደርግ ይሻላል በግሌ ግን እንደማምነው እሳቸው ፈሪሐ እግዚአብሄር ነበሩ በዚያ ላይ ቅን መሪ ስለነበሩና የኃይማኖት ነጻነት ካለገደብ በመፍቀዳቸው የብዙ ሙቶ ሺ ቅዱሳን ፀሎት ደግሞ ስለደገፋቸው በሞገስ ሊመሩ ችለዋል፡፡

**ጥያቄ**፡- ቃለ መሐላ በሚፈፅሙበት ጊዜ ዘላለማዊ ክብር ለጠ/ሚኒስትራችን ያሏት ቃል ብዙ ክርስቲያኖችን ያጠያየቀ ጉዳይ ሆናለች፡፡ ይህችን ቃል ሆን ብለው በርግጥም አምነውባት ነው ያሏት ወይስ የተፃፈልዎትን ነው ያነበቧት?

**ጠ/ሚኒስትር ኃ/መርያም**፡- (ትንሽ ካሰቡ በኋላ) ያንን ንግግር ያዘጋጁት ንግግር አዘጋጆቹ ናቸው፡፡ ግን የንግግሩን ፅንሰ ሀሳብ መጀመሪያ እኔ ነኝ የሰጠኋቸው፡፡ እነሱ ቋንቋውን አሳምረው ቀናንሰውና ጨማምረውበት አስካክተው ኤዲት አድርገው ከጨረሱ በኋላ እኔ ጋር ይደርሳል፡፡ እኔ ሀሳቤን በትክክል ይገልፃል የሚለውን አንኳሩን ክፍል ብቻ አይቼ ያቺን ቃል ሳላስተውል አመለጠችኝና እናም ምንም አማራጭ የለኝም አልኳት፡፡ ማታ ቤት ስመለስ ባለቤቴና ልጆቼ ሁሉ ገና ከበሩ ጀምሮ አተካሩ ገጠሙኝ፡፡ ልጆቼ በተለይ የ16 ዓመቷ ልጄ ያለችው አባ በምድር አላፊ የሆነ ስጋ ለባሽ ከኢየሱስ እኩል በላይ ክብር መውሰድ አይገባውም ብለህ ራስህ አስተምረህን የለም ብላ ስትለኝ በእውነት መልስ አጣሁ፡፡ ትንሽ ፈተና ገጥሞኝ ነበር እልሃለው

**ጥያቄ**፡- እና ተፀፅተዋል ?

**ጠ/ሚኒስትር ኃ/መርያም**:- አዎን... በኋላማ አስቀምጫቸው የሆነውን ነገር ሁሉ አስረድቼያቸው በጠረጴዛ ዙሪያ ሰላም ፈጠርን ፡፡ ግን አንድ ነገር ቤተሰቤም ሆነ መላ ክርስቲያን ወገኖቼ ይረዳሉ ብዬ ተስፋ የማድረገው ነገር እኔ የትናንት የትንሹ ኃ/ማሪያም ቤተሰብ አስተዳደሪና አንድ ተራ የሐዋሪያዊት ቤተክርስቲያን አባልና አማኝ ብሆንም ያንን ማንነቴን ምንም የሚቀይር ነገር የለም፡፡ ጌታ እስከፈቀደ አሁንም ወደ ፊትም ያን የትናንቱን አምላክ ማምለኬ እንደ ግለሰብነቴ ተጠብቆልኝ በአንፃሩ ደግሞ የ80 ሚሊዮን ሕዝብ አደራና ኃላፊነት ስላለ የሁሉንም እምነት እና ኃይማኖት የማክበር ግዴታ አለብኝ፡፡ ሌሎቹም እንዲሁ የእኔን ኃይማኖት ለግሌ ነፃነቴን ትተውልኝ በመቻቻል ተያይዘን በወንድማማችነት በጋራ እንደምንኖር መገንዘብ አለባቸው፡፡ ግን ማንም ኃይማኖቱን ሽፋን አድርጎ ፖለቲካዊም ሆነ ኃይማኖታዊ አድቫንቴጅ ለመውሰድ የማንንም ህሊና መጋፋት እንደሌለበት አምናለሁ፡፡

**ጥያቄ**:- ሌሎች የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች እርስዎ የሚከተሉት እምነት ማለትም «ኦንሊ ጂሰስ ከልት» ነው ወይም አሳች ኃይማኖት ነው ብለው ያምናሉ፡፡ ምናልባት በየኢንተርኔትና በጋዜጦች ተከታትለው እንደሆነ አላውቅም ሰዎች በየቦታው ማንሳታቸው አይቀርምና ስለዚህ ጉዳይ ምን ይላሉ?

**ጠ/ሚኒስትር ኃ/መርያም**:- አሁን ስለ ኃይማኖት ዲኖሚኔሽንና ዶክትሪን ውስጥ ገብቼ ሀሳብ መስጠት አልችልም ፡፡ ምክንያቱም የምነግርህ አንተን ወይም ሌሎቹን የሚያስከፋ ሊሆን የሚችል ሰንሴቲቭ ጉዳይ ስለሆነ እዛ ውስጥ ገብቼ መነጋገር የለብኝም፡፡ ግን አንድ ነገር ማወቅ ያለብን ‹ኦንሊ ጂሰስ› ተከታዮች ብቻ የምንባለው ውሸት ነው በመሰረቱ ኢየሱስ የሚል ስም የኃይማኖታችን ዋናው መሰረት ስለሆነ ይህ ስም የተሰጠን እንጂ እኛም በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ አናምናለን፡፡

**ጥያቄ**:- እርግጠኛ ነዎት የሰማሁት ግን አባትን ከደው  ልጅን ብቻ ያመልካሉ ሲባል ነው?

**ጠ/ሚኒስትር ኃ/መርያም**:- አዎን እርግጠኛ ነኝ፡፡ ይህን ጉዳይ በጥልቀት ለማወቅ ከፈለክ ቤተክርስቲያናችን ወደሚገኝበት ወደ የትም ሄደህ ማረጋገጥ ትችላለህ፡፡ ወይም ... ሳቅ እያሉ ትንሽኛዋ ልጄ ስታገኛት ልታስረዳህ ትችላለች፡፡

**ጥያቄ**:- ባለቤትዎ ወ/ሮ ሮማን ከወላይታ ብሔር አባትና እናት የተወለዱ እንደሆኑ እኔም አውቃለሁ፡፡ ሰሞኑን በኢንተርኔት ግን ኤርትራዊት ናቸው ብለው ወሬ እንደሚናፈስ ሰምተዋል ?

**ጠ/ሚኒትር ኃ/ማርያም**:- (በጣም እየሳቁ) እንደዚህ መባሉን ገና ካንተ መስማቴ ነው፡፡ እኔ ግን የሰማሁት እኔን ነበር ትግሬነት አለበት ሲሉ የሰማሁት ... እንግዲህ ባለቤቴን አንተ ካወካት ሌላ ምን እልሃለው፡፡ እንደገና ግልፅ ማድረግ ካስፈለገ ባለቤቴ ሁለቱም ወላጆቿ የወላይታ ብሄር ተወላጆች ናቸው፡፡ ወላይታ እንግዲህ በኤርትራ ክልል ውስጥ ነው ካልተባለ በቀር እኔም ባለቤቴም ወላይታና ኢትዮጵያዊያን ነን፡፡ ያንን ውዥንብር የሚያናፍሱ የወሬ ፋብሪካዎች መላውን የወላይታ ሕዝብ ዜግነት ጉዳይ ሊወስኑ ነው ማለት ነው፡፡  ዮሃና  ማለት የመፅሐፍ ቅዱስ ስሜ እስከሆነ ድረስ ማንም ባይብል የሚያውቅ ወይም ክርስቲያን የሆነ ሰው መጋራት የሚችለው ስም ነው፡፡ እንኳንስ በቋንቋና በባህል አንድ የሆንን ኤርትራውያን ብቻ ሳይሆኑ ከብዙዎች አገሮች ሕዝቦች ጋር ዩኒቨርሳሊ አንድ የሚያደርገን ክርስትና ነው፡፡ ዮሃና በሉቃስ ወንጌል ሁሉንም ታሪክ ታገኘዋለህ፡፡ የጌታችን ትንሳኤ ካበሰሩት ሴቶች መካከል ከነመግደላዊት ማርያም ጋር ዮሐና የምትባል ሴትም አብራቸው ነበረች፡፡ ትርጓሜውም በእብራይስጥ ቋንቋ የእግዚአብሄር ስጦታ ማለት ነው ለዚህ ነው ይህን ስያሜ የመረጥነው፡፡

**ጥያቄ**:- ንጉስ ጦና አያታቸው ከተምቤን ስለሆኑ ምናልባት የወላይታ ትግሬነት ይኖርብዎታል ብለው እንዳይሆን ?

**ጠ/ሚኒስትር ኃ/ማርያም**:-  እኔ ከጦና ጎሳ አይደለሁም፡፡ ንጉስ ጦና ከሮያል ፋሚሊ ማለትም ‹ካዎናታ› ከሚባል ጎሳ ናቸው፣ እኔ ግን ከዚያ ጎሳ አይደለሁም፡፡

**ጥያቄ**:- ቤት ውስጥ ወላይትኛ ትነጋገራላችሁ? ባለቤትዎና ልጆችዎስ ቋንቋውን በደንብ ይነጋገራሉ ?

**ጠ/ሚኒስትር ኃ/መርያም**:- ወላይታ ውስጥ ተወልደን እስካደግን ድረስ እኔም ባለቤቴም የዘወትር መግባቢያችን ፕራይሜርሊ ወላይትኛ ቢሆንም ግን ብዙ ጊዜ አፋችን ወደሚመራው ቋንቋ እየተጠቀምን እንግባባለን፡፡ ሀሳባችንን በትክክል መለዋወጣችን ላይ እንጂ ሆን ብለን ቋንቋ መርጠን አናውቅም፡፡ የምንገለገልበት ቋንቋ ወላይትኛም አማርኛም አንዳንዴም እንግሊዘኛም ሊሆን ይችላል፡፡ ልጆቻችን የቋንቋችንንና የባህላችን ተካፋይ ሆነው ማደግ ስላለባቸው ቋንቋውን እንዲማሩ ገፋፍተናቸዋል፡፡ ምክንያቱም ከገጠር የሚመጡ ዘመዶቻችን ብዙዎቹ አማርኛ የማይችሉ ስላሉ ከነሱ ጋር መግባባት በመቻላቸው በጣም እንዲቀራረቡ አስችሎአቸዋል፡፡

**ጥያቄ**:-  በአሁኑ ጊዜ በኢህአዴግ አመራር ውስጥ የውጭ አገር ተወላጆች አሉ ስለሚባለውስ?

**ጠ/ሚኒስትር ኃ/መርያም**፡- አሁን አንተ ባለቤቴን ይላሉ እንዳልከው ዐይነት አሉባልታ ነው፡፡ ምንም መሰረት የሌለው ተራ አሉባልታ ነው፡፡ በኢሕአዴግ አመራር ውስጥ ያሉ ታጋዮች አገሬ ናት ስለማይሉትና ለማያምኑበት ዓላማ መተኪያ የሌላትን ሕይወታቸውን አሳልፈው አይሰጡም፡፡ ኢሕአዴግ ከትጥቅ ትግል ዘመን ጀምሮ አንድ ይዞ የመጣ ባህሉ በሙስና የተዘፈቀ (ኮራፕት) የሆነ አባሉን ካለምንም ምህረት እያንጠባጠበ ያጭበረበረ ከተገኘ እያሽቀነጠረ እያጣራ ነው የመጣው፡፡ በአንፃሩ ነባር አመራር ሆነ ዝቅ ያለ ደረጃ ያለ በመልካም ስነ ምግባሩ ከመለካት ባሻገር ማንነቱ ከታወቀ ኢትዮጵያዊ ነኝ ብሎ ሕይወቱን አሳልፎ እስከመስጠት በግንባር የተሰለፈውን ታጋይ በዜግነት ጥርጣሬ ውስጥ ገብቶ የማንንም የዐይን ቀለም የሚመረምርበት ምክንያት የለውም፡፡

**ጥያቄ፡-** በመጨረሻ ክቡር ጠ/ሚኒስትር የሚወዱትን ጥቅስና መዝሙር ቢነግሩኝ?

**ጠ/ሚኒስትር ኃ/መርያም**፡- የምወዳት ጥቅስ ሉቃስ ወንጌል 10፡5 ላይ ኢየሱስ «ወደምትገቡበት ቤት ሁሉ አስቀድማችሁ ሰላም ለዚህ ቤት ይሁን በሉ፡፡ በዚያም የሰላም ልጅ ቢኖር ሰላማችሁ ያድርበታል፣ አለዚያም ይመለስላችኋል፡፡» ያለው ነው፡፡ የእግዚአብሔር ሰላም በውስጣችን ካለ ወደምንሄድበት ሁሉ እሱ ያስቀመጠልንን ሰላም እየዘራን መሄድ አለብን፡፡ የምወዳቸው መዝሙሮች ቢሆኑም

*‹ምን ክብር አለኝ ክብሬ ኢየሱስ ነው፡፡*
*ምን ክብር አለኝ ክብሬ ኢየሱስ ነው፡፡*
*በእሱ ክብር ደግፎ ያኖረኝ*
*በምህረቱ እስካሁንም ያቆመኝ*
*... ክብሬ እለዋለሁ*
*... ሞገሴ እለዋለሁ›*

የሚለው አሁን ምርጫዬ ነው፡፡